April 7, 2009

በጌታ የተወዳችሁ የመካነ ኢየሱስ ካህናት፣ወንጌላዊያንና በተለያየ ዘርፍ አገልጋዮች የነበራችሁ በሙሉ፤ የጌታ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ እያልኩኝ የከበረ ሰላምታዬን በመካነ ኢየሱስ ሰሜን አሜሪካ ቦርድ ስም አቀርባለሁ። ከዚህ ቀጥሎ ያለዉን የጥሪ ደብዳቤ አንብባችሁ ሰዎችን በማስተባበር ከጁላይ 29-እስከ Aug 2, 2009 በ Chicago ወደ ሚደረገዉ አራተኛዉ ዓመት ስብሰባ እንድትመጡ በጌታ ስም አደራ እንላችኋለን። ጌታ ጸጋዉን ያብዛላችሁ።

ጥያቄ ካላችሁ ከመካነ ኢየሱስ ሰሜን አሜሪካ የቦርድ አባላት አንደኛዉን ለመጠየቅ ትችላላችሁ።

የቦርድ አባላት፡-

ቄስ ፍራንሲስ እስጢፋኖስ፣ ስልክ 6123101822፣ franandfetle@yahoo.com
ቄስ ዶ/ር ገመቺስ ደስታ፣ 7736782513, drbuba@gmail.com
ቄስ ዶ/ር ዓለም ሰገድ፣6514974568, pastoralem@trinity-lc.org
ቄስ ያደሳ ዳባ፣6124231997, yadesadaba@hotmail.com
አቶ እንዳልካቸዉ ኪ/ወልድ፣9192011637, endalk@aol.com
ቄስ ብርሃኑ ኦፍጋዓ፣ 6143788501, berhanuof@yahoo.com
ቄስ ዶ/ር እሸቱ አባተ፣ 9493555528፣eshetuabate@hotmail.com

ስለ ሰሜን አሜሪካ መካነ ኢየሱስ ቦርድ

እሸቱ አባተ
ሊቀ መንበር

## 4ኛ ዓመታዊ ኮንፍራንስ

ቀን፡- ከ July 29 (Wednesday) እስከ August 2 (Sunday), 2009.

ቦታ፡- Chicago, ILL

አድራሻ፡- St. Peter's Lutheran Church

202 East Schaumburg Road,

Schaumburg, Illinois 60194-3593

Hosts:- Chicago Mekane Yesus

& St. Peter's Lutheran Church

Contacts:- Ato Solomon Haile, Tel. 8478430679 or 2243539013

Qes Tadesse Kassa:- 8474594467 or 8474099660 cell

ማብራሪያ:-

በ April 3-4, 2009 የመካነ ኢየሱስ አባላት ኅብረት ቦርድ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ በ St. Peter's Lutheran Church, Schaumburg, ILL ከ ቺካጎ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መሪዎችና አባላት እንዲሁም ከ St. Peter's Lutheran Church መሪዎች ጋር አስደሳችና ጠቃሚ ስብሰባ አድርጎ ነበር፡፡ ቦርዱ በግሉና በጋራ ባደረጋቸዉ ስብሰባዎች የሚከተሉት ዉሳኔዎችና ግንዛቤዎችን አድርጓል፡፡

1. የስብሰባዉ መሪ ቃል፡- ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሐሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን›› ፊልጵ 2፡5 የሚል ነዉ፡፡ ዝርዝር ፕሮግራም ወደፊት ይገለጻል፡፡

2. በስብሰባዉ በአገራችን በመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን የተደረገዉን እርቅ በማስመልከት በቪድዮ የተደገፈ መግለጫ ይሰጣል፡፡ በዚያ ላይ በመመርኮዝ

እዚሁም አገር በክርስቶስ ኢየሱስ የማስታረቅ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ የንስሐ፣የእርቅና የአንድነት ጊዜ ይኖረናል። በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ በርካታ የቀድሞ መካነ ኢየሱስ ፕሮዝደንቶችና መሪዎች ይገኛሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

3. በስብሰባዉ በሰሜን አሜሪካ ለሚገኙ የመካነ ኢየሱስ ቄሳዉስት፣ ወንጌላዊያንና አገልጋዮች በሙሉ የአንድ ቀን ትምህርታዊ ሠሚናር ተዘጋጅቷል።

4. ለአገልጋዮች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ምእመን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያካፍሉ አገልጋዮች ተመድበዋል።

5. ማደሪያ፡- የ St. Peter's Lutheran Church, Schaumburg, ILL, ሦስት ሺህ አባላት ያሉት (3000) ትልቅ ቤተክርስቲያን በመሆኑ በቅጥረ ግቢዉ ከሚያመልኩ የመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን አባላት ጋር በመሆን እንግዶችን በሙሉ በቤታቸዉ ለማስተናገድ ፈቃደኞች ሆነዋል። ለምሳሌ ያክል የቤተክርስቲያኗ ዋናዉ ካህን በቤታቸዉ ከቁርስ ጋር ስድስት ሰዎችን ለማሳደር ፈቃደኛ መሆናቸዉን ገልጸዉልናል። የዚህ ዓይነት መስተንግዶ በዓለም የማይገኝ በክርስቶስ ያለንን አንድ አካልነትንና ፍቅርን የሚያሳይ በመሆኑ በራሱ ትልቅ መልእክት ይሆናል።

በቤታቸዉን ለዚህ አገልግሎት በከፈቱ የመካነ ኢየሱስ አባላትና በክርስቶስ አንድ አካል ለሆኑ የ St. Peter's Lutheran Church አባላት ዘንድ <u>ሰዎችን መመደብ እንችል ዘንድ የምትመጡ ሰዎች ከMay 15, 2009 በፊት መምጣታችሁን በአስቸኳይ እንድታስታዉቁን በትሕትና እንጠይቃለን።</u> የምትመጡት ለብቻችሁ ይሁን ወይም ከባለቤቶቻችሁ ግልጽ አድርጉልን። ልጆችም ካላችሁ ስንት እንደሆኑ ግልጽ አድርጉልን።

መልእክታችሁን፡- በe-mail:- solomond@awana.org with a copy to eshetuabate@hotmail.com መላክ ትችላላችሁ።

በተጨማሪ፡- ተያይዞ በ Attachment የተላከዉን ቅጽ ሞልተዉ ሊሊኩ ይችላሉ።

6. መጓጓዣ፡- እያንዳንዱ ከሚኖርበት ሥፍራ የራሱን ወጪ ችሎ ወደ ኮንፍራንሱ ቦታ ይደርሳል። በአይሮፕላን የምትመጡ አስቀድማችሁ

የምትመጡበትን Airline, Flight No, Date and time, እንድታሳዉቁ ያስፈልጋል።

7. ምግብ፦ ለአንድ ሰዉ በቀን ከ 10 ዶላር በላይ ወጪ እንዳይኖር ኮሚቴዉ ጥረት ያደርጋል።

8. Chicago, ILL ማዕከላዊ ቦታ በመሆኑ፣ ከብዙዎቹ States በአንድ ቀን ጉዞ በመኪና ስለሚደረስ በርካታ የመካነ ኢየሱስ መሪዎችና አባላት ይመጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በሩቅ ያሉ ደግሞ በዚህ ታላቅ የአንደነት ስብሰባ ላይ ለመገኘት በአይሮፕላን ይመጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ቄስ ዶ/ር እሸቱ አባተ

ስለ ማኅበሩ